ይድረስ ለጀርመን ድምፅ ያማርኛው አገልግሎት
ቦን

በተቀዳሚ ስላምታችን ይድረሳችሁ።

ቀጥሎም እ.አ.አ በ23.03.2017 ዓ.ም የዜና መጽሔት ትንተናቹሁ አራት የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ማለትም የኦሮሞ አቦ ግንባር፣ የኦሮሞ ነፃነት አንድነት ግንባር፣ የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ፣ የኦሮሞ ነፃነት ብሔራዊ ፓርቲ ከተሰኙት ሁለት ተወካዮች ቀርበው አዲስ አበባ ከተማን የኦሮሚያ ክልልና የአዲስ አበባ አስተዳደር በጋራ እንዲያስተዳድሩዋት እንዲሁም ባለፉት 25 ዓመታት ከከተማዋ የተፈናቀሉ የኦሮሞ ተወላጆች ካሣ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል።

ያለ ኢትዩጵያ ሕዝብ ተሳትፎና ይሁንታ በወያኔ ትግሬ ሕወሐትና ተለጣፊዎች የተዘጋጀውን የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ፌደራሊዝምና ሕገ መንግሥት ተብዬው መሠረት የኦሮሚያ ክልል ከአዲስ አበባ ማግኘት የሚገባውን ልዩ ጥቅምና ባለቤትነት ለማስከበር፣ በአዲስ አበባ የኦሮሞን ባሕልና ቋንቋ ለማስፋፋት ማቀዳቸውን ተወያዮች ገልጸዋል።
የሚያስገርመው አወያዩ ወይም ጠያቂው የጀርመን ድምፅ ጋዜጠኛ የተነገረውን እንዳለ እንደወረደ አናፈሰ እንጂ የአዲስ አበባን ሕዝብ የማንም መጠቀሚያና ልዩ ሃብት ያለመሆኑንና ራስን በራሱ የማስተዳደር መብትና ነፃነት ያለው መሆኑን አላገናዘበም። ስለሆነም ነው ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ የተገደድነው።

በግልጽ እንደሚታወቀው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ሕዝብ በቅጥረኛው ወያኔ ትግሬ አናሳ ጎሣና ተለጢፊዎቹ ኢዲሞክራሲያዊ አምባገነን የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካ ሰለባ ነው። ሕዝቡ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብትና ነፃነቱን ተገፏል፤ የራሱን ከንቲባና አስተዳዳሪዎች መምረጥ አይችልም። ይባስ ተብሎም በየጊዜው ከቤት ንብረቱ በወያኔ ወራሪ ታጣቂዎች እንበለ ፍትሕ ከየክፍለ ከተማው የሚፈናቀለው ሕዝብ ቁጥር በጣም ከፍተኛ ነው።
ጥቂት ወያኔ ትግሬዎችና ግብረበላዎቹ በአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ኪሣራ ሲንደላቀቁና በምቾት ቅንጦት ሲምነሸነሹ የአብዛኛው አዲስ አበቤ ኑሮ ከሞቱት በላይ፣ ከቁሙት በታች እንድሆነ የተረጋገጠ ነው።
ታዲያ! በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ እራሳቸውን የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚሉት ጠባብ ጎሠኞች የአዲስ አበባን ሕዝብ የራስን በራስ ማስተዳደር ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብት ተላልፈው ከተማዋ በኦሮሚያ ክልል ተብዬው ሥር እንድትሆን ይፈልጋሉ። አልፈው ተርፈውም ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ኦሮሞሦች ዘር ማንዘራቸው ተፈልጎ ካሳ ይገባቸው ነበር ያሉት እነዚ ፓርቲዎች አሁን ግን ቢያንስ በ25 ዓመቱ የኢሕአዴግ ዘመን ከከተማዋ የተፈናቀሉት ገበሬዎች ከያለበት ተሰብስበው ተገቢ ካሣ እንዲከፈላቸው ማሳሰባቸው ታውቋል።
ከዚህ ጋራ በተያያዘ የናዝሬት ከተማን ሁኔታ ማገናዘብ ያስፈልጋል። ናዝሬት የኦሮሚያ ክልል ተብዬው ዋና መዲና ናት ይባላል።

ነገር ግን ከነዋሪዎቹዋ 75 በመቶ እጅ ዐማርኛ ተናጋሪዎች ቢሆኑም እንኳ ዐማሮች በራሳቸው ፊደልና ቋንቋ እንዳይጠቀሙ ተከልክለዋል፤ በግዳጅ ጥቁር ፈረንጅ እንዲሆኑ ተደርጎ በቁቢ ላቲን ፊደልና በኦሮምኛ ቋንቋ ማመልከቻ እንዲጽፉ ይገደዳሉ።
በአጠቃላይ ከፖለቲካውና ኢኮኖሚው ዘርፍ የናዝሬት ከተማ ነዋሪ ዐማሮች በሁለተኛ ደረጃ ዜግነት የተገለሉ ናቸው። የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቴዎች የሚፈልጉት አዲስ አበባን በቁጥጥር ሥር አድርገው የናዝሬትና ሌሎች ከተሞች ልምዳቸውን መተግበር ነው።

የኦሮሞ ጎሣ ብሔረተኞች በግልጽ ሊገነዘቡት የሚያስፍልግ ዐቢይ ነገር አለ። ከሁሉ በተቀዳሚ አዲስ አበባ የሸዋ ክፍለ ሀገር ዋና ከተማ ናት። የወረሞ ጎሣ ብቻ ልዩ ሃብት አልነበረችም፣ አትሆንም። አዲስ አበባ (እንዶጥና) በመናገሻ አውራጃ ውስጥ የምትገኘው የኢትዩጵያ መዲና ከኦሮሞ (ጋላ) የ17ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ከጥንት ጀምሮ ያማራ፣ የከምባታ፣ የሃድያ፣ የዳሞት፣ የጉራጌና ጋፋት ሕዝብ ምድር በሆነው ሸዋ ውስጥ ነው። ስለሆነም አዲስ አበበባ በመናገሻ አውራጃ በአራቱም ማዕዘናት መስፋት ትችላለች። አባሪ ካርታውን ይመለከቷል።
ካሳ መክፈል ያለባቸውማ በሉባ የደፈጣ ውጊያ ስልት ከኬኒያ ቦረና ጠርፍ ተነስተው በሸዋና ዙሪያ የስፈሩት የወረሞ ጎሣዎች ናቸው።
የወረሞ ጠባብ ጎሥኞች ከወያኔ ትግሬና ሻዕቢያ ጋራ ሆነው ከሐረርጌ፣ ከአሩሲ፣ ከወለጋ፣ ከደቡብ ሸዋ፣ ከባሌ፣ ከኢሉባቦር ወዘተረፈ ያማራ ተወላጅ ገበሬዎችን፣ ሠራተኞችን ጨፍጭፈዋል፣ ሃብት ንብረት ዘርፈዋል። በጎሣ ማጥፋትና ማጥራት ለተፈናቀሉት በሚሊዎን ለሚቆጠሩት ዐማሮችስ ለምን ካሳ አይከፈላቸውም?
ሌላው ደግሞ በአዲስ አበባ ዙሪያ የተፈናቀሉት ገበሬዎች ወረሞች ብቻ አስመስሎ ማናፈሱ ነው። በአዲስ አበባ ሆነ በዙሪያዋ ከተፈናቀሉት ውስጥ ዐማሮችም በብዛት ይገኝበታል። አፈናቃዩችም ኦሮሞ የሆኑት የወያኔ ትግሬ ቅልቦችና ተላላኪዎች ናቸው።

የሸዋ ነገሥታት በተለይም አጤ ምኒልክ የጥንት አገራችን በደቡብና በምሥራቅ በከፊል ብቻ አስመልሰዋል። እነ በርበራና ዘይላ በአውሮፓ ቅኝገዥዎች ተይዘው ሳይመለሱ ቀርተዋል።

የሸዋ ሕዝብ ድርጅት (ሽሕድ )
Shoa People Organization ( SPO)
WWW.shoa.org